የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአጠቃላይ ትምህርት ጥራትና አግባብነት ሬጉላቶሪ ኤጀንሲ

የአፀደ ህጻናት፣ የመጀመሪያ ደረጃና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ተቋማት

የዕውቅና ፈቃድ አሰጣጥና ዕድሳት የአፈጻፀም መመሪያ

የካቲት 2008 ዓ.ም

አዲስ አበባ

መግቢያ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መንግስታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶችና በሀገር ውስጥ የግል ባለሀብት የሚቋቋሙ የትምህርት ተቋማት የሚካሄዱት የመማር ማስተማር ተግባራት የሀገሪቱን የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ መሠረት በማድረግ ስርዓተ ትምህርቱን የተከተሉ እንዲሆኑ ፣

በትምህርት ተቋማቱ የሚያካሄዱት የመማር ማስተማር ተግባራት በአጠቃላይ ከሀገራዊ የትምህርት ዓላማና ተልዕኮ አኳያ መካሄድ ያለበት ከመሆኑ በተጨማሪ የከተማውን ተጨባጭ ሁኔታ ፣ራዕይና ዓላማና ተልዕኮ ያገናዘበ መሆን ያለበት በመሆኑ፣

የትምህርት ተቋማቱ በሚፈለገው ደረጃና ብቃት ትምህርት እንዲሰጡ ለማስቻል በሚመለከተው የመንግስት አካላት እየተገመገሙ ተገቢውን የትምህርት ስታንዳርድ ሲያሟሉ የዕውቅና ማረጋገጫ በመስጠትና የዕውቅና ማረጋገጫ ከተሰጣቸው በኋላም ቢሆን ይህንኑ የማስተማር ተግባር በአግባቡ እያከናወኑ መሆኑን ክትትል፣ድጋፍና ቁጥጥር በማድረግ ተገቢውን ውሳኔ መስጠት አስፈላጊ በመሆኑ፣

በአጠቃላይ የሀገሪቱን የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲውን ዓላማና ተልዕኮ ለማሳካት ለትምህርት ተቋማት ተገቢውን የዕውቅና ማረጋገጫና ዕድሳት ፈቃድ አሰጣጥን አፈጻፀምን በመመሪያ የታገዘ እንዲሆን አስፈልጓል።

ስለሆነም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በተሸሻለው ቻርተር 361/1993 እና በአዋጅ ቁጥር 35/2004 የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ በአንቀጽ 9 ተራ ቁጥር 2 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል።

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1.1 አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ " የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአጠቃላይ ትምህርት ጥራትና አግባብነት ሬጉላቶሪ ኤጀንሲ የአፀደ ህጻናት፣ የመጀመሪያ ደረጃ፣ የሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤቶች የዕውቅና ማረጋገጫና ዕድሳት አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር..../2008 ዓ.ም ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

1.2 ትርጉም

በዚህ የአፈፃፀም መመሪያ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፥-

1.2.1 “ኤጀንሲ“ ማለት- በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአጠቃላይ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ሬጉላቶሪ ኤጀንሲ ነው፣

1.2.2 የኤጀንሲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ማለት ተጠሪነታቸው ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትምህርት ጥራትና አግባብነት ሬጉላቶሪ ኤጀንሲ የሆኑ በክፍለ ከተማ ደረጃ የተቋቋሙየኤጀንሲው ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ማለት ነው

1.2.3“ትምህርትቤት/ተቋም /”ማለትበሚመለከተው አካል ፈቃድ ተሰጥቶ ትምህርት በመስጠት ላይ የተሰማሩ የአፀደ ህጻናት /ቅድመ መደበኛ/፣የመጀመሪያ ደረጃ፣የሁለተኛ ደረጃና የመሰናዶ የመንግሥት ወይም የግል የትምህርት ቤት/ ተቋም/ ነው።

1.2.4. “የግል ትምህርት ተቋም” ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ስር የሚተዳደር በግለሰቦች፣በማህበራት ወይም በበጎ አድራጎት ድርጅት የተቋቋመ ተቋም ሲሆን ከቅድመ-መጀመሪያ ደረጃ እስከ መሰናዶ ደረጃ ድረስ መደበኛ ትምህርት የሚሰጥበት ተቋም ነው።

1.2.5 “አጠቃላይ ትምህርት“ ማለት- የአፀደ ህጻናት /ቅድመ መደበኛ/፣የመጀመሪያ ደረጃ፣የሁለተኛ ደረጃና የመሰናዶ ትምህርትን የሚሰጥ የትምህርትን ዘርፍ ነው፣

1.2.6 “የትምህርት አገልግሎት” ማለት መንግስት ያወጣውን የሥርዓተ ትምህርት ማዕቀፍ ተከትሎ የሚሰራ የመማር ማስተማር እና ተያያዥ አገልግሎትን የመስጠት ስራ ነው።

1.2.7 “የትምህርትጥራት” ማለት ተገቢውን መመዘኛ ያሟላ ፣ ደረጃውንና ብቃቱን የጠበቀ እውቀትና ክህሎት የሚያስጨብጥ ትምህርት ነው።

1.2.8 “የእውቅና ፈቃድ” ማለት በመማር ማስተማር ተግባር ላይ ለመሰማራት የተዘጋጀውን የትምህርት ስታንዳርድ አሟልቶ በመገኘቱ የትምህርት ጥራትና አግባብንት በኤጀንሲው ባለሙያዎች የሚሰጥ የብቃት ማረጋገጫ ነው።

1.2.9 “የትምህርት ስታንዳርድ (standard)” ማለት የትምህርት ጥራትና አግባነት ለማረጋገጥ የተቋማት አደረጃጀትና ዝግጅት ፣ የመምህራንና የትምህርት አመራሩ የትምህርት ዝግጅትና ሌሎች የትምህርት ግብዓትን ለመለካት የሚያስልች ልኬት ማለት ነው።

1.2.10 “ደረጃ ማሳደግ” ማለት አንደ ተቋም ቀደም ሲል ባገኘው የእውቅና ፈቃድ ላይ በተጨማሪ ካለበት የትምህርት

እርከን ወደቀጣዩ የትም/እርከን ከፍ አድርጐ መክፈት ማለት ነው።

1.2.11“ዕድሳት” ማለት አንድ እውቅና የተሰጠው የትምህርት ተቋም በደንቡ በተገለፀው የጊዜ ገደብ መሠረት የእውቅና ፈቃዱን ማደስ ማለት ነው።

1.3 የጾታ አገላለጽ

በዚህ መመሪያ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸ ቃል ወይም አባባል የሴትንም ጾታያካትታል።

1.4 የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በሚገኙ የትምህርት ተቋማት ማለትም በአጸደ ሕጻናት ፣በመጀመሪያ ደረጃ ፣ በአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃና በመሰናዶ ትምህርት ቤቶች ላይ ተፈጻ ሚይሆናል።

1.5 የመመሪያው ዓላማዎች

የመመሪያው ዋና ዓላማ በልማታዊ ባለሀብቶች በግል የሚከፈቱ የትምህርት ተቋማት በትምህርት ስታንደርዱ መሠረት የሚጠበቅባቸውን አጥጋቢ መስፈርት (Minimum Requirements) አሟልተው መገኘታቸውን በማረጋገጥ ደረጃቸውን የጠበቀ የትምህርት ተቋማትን የማስተማር ዕውቅና ፈቃድ መስጠት የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት መዘረጋት ሲሆን የሚከተሉትን ዝርዝር ዓላማዎች አካቷል፦

1.5.1 ትምህርት ቤቶች ለደረጃው የሚጠበቅባቸውን አጥጋቢና ተፈላጊ ብቃት እንዲኖራቸው በግብዓት መሟላታቸውን ለማረጋገጥ፣

1.5.2 የግል ባለሀብቱን በአጠቃላይ የትምህርት ዘርፍ የሚያደርገውን የኢንቨስትመንት ስራ ለማበረታታት፣

1.5.3 ትምህርት ቤቶች የማስተማር ፈቃድ ከማግኘታቸው በፊት በባለሙያ ተገምግመው የተጠየቀው የትምህርት ደረጃ በሚፈለገው ግብዓትና ብቃት ትምህርቱን መስጠት የሚችል መሆኑን፣ እንዲሁም በየጊዜው በመከታተል ማሻሻልና ማስተካከል የሚገባውን መፈፀሙን በማረጋገጥ የዕድሳት ፈቃድ መስጠት የሚያሥችል አሰራር መፍጠር

1.5.4 ትምህርት ቤቶች የማስተማር ፈቃድ እንዲሁም የዕድሳት ፈቃድ ወይም የደረጃ ማሳደግ ጥያቄን ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል ሁኔታዎችን ለማመቻቸት፣

1.5.5 የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ፓኬጅ በተለይም የትምህርት ቤት ማሻሻያ መርሃ-ግብርን አተገባበርን ለመተግበር የሚያስችል አሰራርን ለመፍጠር፣

1.6 የመመሪያው አስፈላጊነት

በየደረጃው የሚገኙ የትምህርት ተቋማት (በአፀደ ሕፃናት፣ በመጀመሪያ ደረጃ ወይም በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች) የሚሰጡ ትምህርቶች ጥራታቸውን የጠበቀ አግባብነት መሆናቸውን እንዲሁም በአጠቃላይ ከአገሪቱ ትምህርት ስትራቴጂ፣ ሀገር አቀፉንና

የከተማው ስርዓተ ትምህርት ማዕከል ያደረገና የተገናዘበ ትምህርት መሰጠቱን ለማረጋገጥ እንዲቻል መመሪያ ማዘጋጀት አስፈላጊ በመሆኑ ነው ።

1.7 የተቋማት ዕውቅናና ዕድሳት ፈቃድ አሰጣጥ መርሆዎች

- የሀገሪቱ ሕገ መንግስት የሚደነግጋቸውን መሠረታዊ የዜጎችና የሕዝቦች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች የመጠበቅና የማስጠበቅን አመለካከትና ኃላፊነት የወሰደ ተቋም መፍጠር፣
- በማኅበረሰቡ ውስጥ ገንቢና አዳዲስ አስተሳሰቦች እንዲንሰራፉ፣ እውቀት የሚዳብርበትንና የሚስፋፋበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣
- በትምህርት ዘርፉ ተገቢ እሴቶች በማስረጽ አመለካከትና አሰራሮችን ማሻሻልና ለዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታ መንቀሳቀስ፣
- የኃይማኖትና ከፖለቲካ ወገንተኝነት የነፃና የዘር፣ የኃይማኖት፣ የቀለምና የፆታ ልዩነት የሌለበት የትምህርት አገልግሎት መስጠት፣
- ሀገራዊና ክልላዊ ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን ባገናዘበ መልኩ የማኅበረሰቡን ችግሮች የሚፈቱ፣ ለልማትና እድገት ግንባታ ፋይዳ ያላቸውን ጥናትና ምርምሮችን በማካሄድ ውጤቱን ለተጠቃሚዎች ማስተዋወቅ፣
- የዲሞክራሲን መርሆዎች በክፍል፣ በት/ቤትና በማህበረሰቡ ውስጥ የሚተገብሩ ተማሪዎችን ማዘጋጀት የሚችል ተቋም ሆኖ መገኘት፣
- በትምህርት ማኅረሰቡ፣ በአካባቢ ህብረተሰብና ህዝቦች መካከል የመከባበር፣ የመቻቻልና አብሮ የመኖር ባሕልን ማጐልበት ።

ክፍል ሁለት

2.1 አደረጃጀት

ሀ/ የአፀደህጻናትና የመጀመሪያ ደረጃ የትምህርት ተቋማት ዕውቅና ፈቃድ አሰጣጥና ዕድሳት በክፍለ ከተማ የኤጀንሲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ይሆናል፣

ለ/የሁለተኛ ደረጃና የመሰናዶ የትምህርት ተቋማት ዕውቅና ፈቃድ አሰጣጥና ዕድሳት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኤጀንሲ ይሆናል፣

2.2 የትምህርት ተቋማት ዕውቅናፈቃድ አሰጣጥና ዕድሳትሥርዓትና ይዘት

ሀ/ማንኛውም አዲስ የትምህርት ተቋም ለመክፈት፣ የኘሮግራም ለውጥ ለማድረግ ወይም ደረጃ ለማሳደግ የሚፈልግ ግለሰብ ወይም የትምርት ተቋም የትምህርት አገልግሎት መስጠት ከመጀመሩ በፊት በትምርት ዘመኑ ከመጋቢት 30 እስከ ሰኔ 30 ወር ድረስ ብቻ፣ ለሚመለከተው የፈቃድ ሰጪ አካል ጥያቄ አቅርቦ ተገምግሞና ብቁ ሆኖ ሲገኝ የእውቅና ፈቃድ ማግኘት ይጠበቅበታል።

ለ/ማንኛውም የትምህርት ተቋም እውቅና ሳያገኝ ተማሪዎችን መዝግቦ ማስተማር መስጠት አይችልም። እውቅና ሳያገኝ ትምህርት ሲሰጥ የተገኘ ትምህርት ተቋም በህግ ተጠያቂ ይሆናል።

ሐ/የእውቅና ፈቃድ እንዲሰጠው ጥያቄ ላቀረበ ማንኛውም አካል በጥያቄው ተካተው የቀረቡትን የቅድመ ሁኔታ መረጃዎች አሟልቶ ካቀረበ በኋላ የዕቀውቅና ፈቃድ ሰጪ ባለሙያዎች በተቋሙ በመገኘትና በመገምገም መስፈርቱን (Standard) ማሟላቱ ከተረጋገጠ በ 8 ሰዓት ጊዜ ውስጥ የእውቅና ፈቃድ ማረጋገጫ ይሰጠዋል።

መ/ የእውቅና ፈቃድ ማረጋገጫው ለ 2 ዓመት ጊዜ የሚቆይና የሚያገለግል ይሆናል።

ሠ/ ማንኛውም እውቅና የሌለው ትምህርት ተቋም እውቅና ሳያገኝ የሚሰጠው የትምህርት ማስረጃ ተቀባይነት አይኖረውም ።

ረ/ የእውቅና ፈቃድ ያለው ትምህርት ተቋም የትምህርት አገልግሎቱን ከተሰጠው ደረጃ በላይ ለማሳደግ ሲጠይቅ መስፈርቱን ስለማሟላቱ በባለሙያዎች ሲረጋገጥ እውቅና ይሰጠዋል።

ሰ/ ማንኛውም የትምህርት ተቋም በመደበኛው ፕሮግራም ከተፈቀደለት የትምህርት ደረጃ ወይም ከማያስተምረው የትምህርት ዘርፍ ውጪበማታው ክፍለ ጊዜ ማስተማር አይቻልም፣

ሸ/ ተቋሙ ዕውቅና አግኝቶ እየሠራ ካለበት ቦታ በተጨማሪ በሌላ ቦታ ቅርንጫፍ ለመክፈት ከፈለገ እንደማንኛውም ተቋም እንደአዲስ የእውቅና ጥያቄ ባለበት አድራሻ የሚጠይቅ ይሆናል።

ቀ/ የማስተማሪያ ቦታውን የሚቀይር የትምህርት ተቋም ቀደም ሲል ባገኘው እውቅና መገለገል አይችልም።

በ/ አንድ ተቋም የሚያስተምርበትን ቦታ ሲቀይር በሚቀይርበት ቦታ ለሚገኘው ዕውቅና ሰጪ አካል የዕውቅና ጥያቄውን በማቅረብ ዕውቅና ማግኘት አለበት።

ተ/ ተቋሙ ከነበረበት በተለየ ቦታ ቅርንጫፍ ለመክፈት ከፈለገ እንደማንኛውም ተቋም እንደ አዲስ የእውቅና ጥያቄ ባለበት አድራሻ የሚጠይቅ ይሆናል

ቸ/ የዕውቅና ሰጪው አካል ማንኛውም ትምህርት ተቋም የተፈቀደለትን የትምህርት ደረጃ በተጨማሪም የደረጃ ማሳደግ ዕውቅና ሲያገኝ የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ለማህበረሰቡ እና ለተጠቃሚዎቹ ያሳውቃል።

2.3 የዕውቅናና ዕድሳት ፈቃድ ጥያቄ አቀራረብ

2.3.1 የትምህርት አገልግሎት ለመስጠት በሀገር ውስጥ የግል ባለሀብት ወይም በሀገር በቀል መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ወይም በማህበራት የሚቋቋም ትምህርት ተቋም የእውቅና ፈቃድ እንዲሰጠው አፀደ ሕፃናትና መጀመሪያ ደረጃ ከሆነ ጥያቄውን ለክፍለ ከተማ የኤጀንሲው ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ፣ ሁለተኛ ደረጃ /9-12/ ከሆነ የአጠቃላይ ትምህርት ጥራትና አግባብነት ሬጉላቶሪ ኤጀንሲ ለሚመለከተው ለእውቅናና ዕድሳት ፈቃድ ሰጪ ዘርፍ ማቅረብ ይኖርበታል።

2.3.2 በውጭ ሀገር ባለሀብቶች፣ በውጭ ሀገር ህግ መሠረት የተቋቋሙ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና በፌዴራል መንግስት አካላት የሚተዳደሩ ተቋማት የትምህርት አገልግሎት ለመስጠት የሚፈልጉ የእውቅና ጥያቄያቸውን ለትምህርት ሚኒስቴር ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል ።

2.4 ከዕውቅና ጥያቄ ማመልከቻ ጋር ተያይዘው ሊቀርቡ የሚገባቸው ሰነዶች

የእውቅና ማመልከቻ ጥያቄ ሲቀርብ የሚከተሉት ሰነዶችን አብሮ መቅረብ አለባቸው።

ሀ. ለዕውቅና ፈቃድ ጥያቄ ማቅረቢያ የተዘጋጀውን ማመልከቻ ቅፅ መሙላት

ለ. የትምህርት ተቋም ባለቤት ስምና አድራሻ

ሐ. የተቋሙ ተጠሪ የሆነው አካል ስምና አድራሻ

መ. የተቋሙ ራዕይ፣ ተልዕኮና ዓላማዎች፣ የተቋሙ የ 3 ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ

ሠ. ተቋሙን ለማቋቋም የሚያስችሉና አግባብ ባለው መዝጋቢ መ/ቤት (ውልና ማስረጃ) የተመዘገበበት የተቋሙ መመስረቻ ሠነድ፣ ማህበር ከሆነ የማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ ቅጂ።

ረ. የተቋሙ አካዳሚያዊና አስተዳደራዊ ሥራዎች የሚከናወንበት የአመራር አደረጃጀት የሚያስረዳ መተዳደሪያ ሰነድ/legislation/

ሰ. በተቋሙ የሚገኙ ልዩ ልዩ የአገልግሎት መስጫ ክፍሎች በስታንዳርዱ መሰረት በሰው ሀይል በማቴሪያልና በሌሎች የትምህርት ግብዓት በአግባቡ የተደራጁና ደረጃውን የጠበቀ አደረጃጀት፣

ቀ. ተቋሙ ለትምህርት አገልግሎት የሚጠቀምባቸው መሳሪያዎችና ዕቃዎች ዝርዝር፣ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ፣ልዩ ልዩ ደንቦችና መመሪያዎች ፣የትምህርት ሲለበስና ማዕቀፎች ፣የአጠቃላይ ትምህርት ማረጋገጫ ፓኬጅ ወዘተ

በ. የቋሚ እና የኮንትራት መምህራንና የአስተዳደር ሠራተኞች ዝርዝር የቅጥር ውል የጽሁፍ ማስረጃ ኮፒ እንዲሁም በውልና ማስረጃ የፀደቀ የስራ/ኮንትራት/ ውል።

ተ. አዲስ ወይም የታደሰ የኢንቬስትመንት ፈቃድ፣

ቸ. ተቋሙ የራሱ የሆነ ህንጻ የሌለው ከሆነ ቢያንስ ለሦስት ዓመት ህጋዊ የኪራይ ውል በአግባቡ ተሞልተው መቅረብ አለባቸው።

2.5 የእውቅና ፈቃድ አሰጣጥ

ሀ/ የእውቅና ፈቃድ እንዲሰጠው ጥያቄ ላቀረበ ማንኛውም አካል በጥያቄው ተካተው የቀረቡትን የቅድመ ሁኔታ መረጃዎች አሟልቶ ካቀረበ በኋላ የዕቀውቅና ፈቃድ ሰጪ ባለሙያዎች በተቋሙ በመገኘትና በመገምገም መስፈርቱን (Standard) ማሟላቱ ከተረጋገጠ በ 8 ሰዓት ጊዜ ውስጥ የእውቅና ፈቃድ ማረጋገጫ ይሰጠዋል።

ለ/ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የት/ቤቱን ቦታ የሚቀይር የትምህርት ተቋም ሁኔታውን ለእውቅና ሰጪው አካል አሳውቆ የአገልግሎት ክፍያ በመክፈልና እንደገና በማስገምገም ይስተናገዳል።

ሐ/ የእውቅና ሰጪው አካል ማንኛውም ትምህርት ተቋም የተፈቀደለትን የትምህርት ደረጃ በተጨማሪም የደረጃ ማሳደግ እውቅና ሲያገኝ በተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ለማኅበረሰቡ እና ለተጠቃሚዎቹ ያሳውቃል።

መ/ ተቋሙ ባቀረበው ማመልከቻ መሠረት እውቅና ሲፈቀድለት የሚጠበቅበትን የአገልግሎት ክፍያ ገቢ የተደረገበት ደረሰኝ ማቅረብ አለበት።

2.6 የእውቅና ፈቃድ ማረጋገጫ ይዘት

ፈቃድ ሰጪው አካል የሚሰጠው የእውቅና ፈቃድ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚከተሉትን ማካተት አለበት፦

- የትምህርት ተቋም ሥም፣
- ተቋሙ የሚገኝበትን ቦታ፥ አድራሻ/ክ/ከተማ፣ ወረዳ፣ የቤት ቁጥር/
- የተፈቀደለትን የትምህርት ደረጃ ፣ እርከን፣
- ፈቃዱ የተሰጠበት ቀንና
- ፈቃዱ ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ የመጨረሻ ቀን፣
- የእውቅና ፈቃድ በማረጋገጥ የምስክር ወረቀቱን ያዘጋጀው ባለሙያ ስም እና ፊርማ
- በምስክር ወረቀቱ ላይ እንዲፈርም ስልጣን የተሰጠው ሀላፊ ስም እና ፊርማ
- የእውቅና ፈቃድ ሰጪው አካል ክብ ማህተም መያዝ አለበት።

ክፍል ሦስት

3.1 ክትትልና ድጋፍ መስጠት

ሀ/ እውቅና ሰጪው አካል ለተቋሙ የማስተማር ፈቃድ ከሰጠ በኋላ በማንኛውም ጊዜ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ተቋሙ ደረጃውንና ብቃቱን የጠበቀ የትምህርት አገልግሎት መስጠቱን ማረጋገጥ አለበት።

ለ/ተቋሙም እውቅና ሰጭው አካል በማንኛውም ጊዜ ለሚያደርገው ክትትልና ድጋፍ አስፈላጊውን ትብብርና ምቹ ሁኔታን የመፍጠር ግዴታ አለበት፥

ክፍል አራት

4.1 የእውቅና ፈቃድ ስለማደስ፣ ምትክ ስለመስጠት፣ ስለመሰረዝ እና ስለመመለስ

4.1.1 የእውቅና ፈቃድን ስለማደስ፣

ሀ/ ዕውቅና የተሰጠው ማንኛውም የትምህርት ተቋም የእውቅና ፈቃዱ ለሁለት ዓመት ፀንቶ ይቆያል፣ ይህ የዕውቅና ጊዜ ከመጠናቀቁ ከሦስት ወራት ዕውቅናው እንዲታደስለት ለፈቃድ ሰጪው አካል በጽሁፍ ማመልከት አለበት።

ለ/ የዕውቅና ፈቃድ እድሳት መጠየቂያ ማመልከቻ ሲቀርብ ተቋሙ በዕውቅና ፈቃድ ወቅት የነበረው የስራ እቅስቃሴ ፣የስራ አፈጻፀም ፣ የተቋቋመበትን ዓላማዎቸች ለማሳካትና ዕውቅና ሰጪው አካል ያስቀመጣቸው ተቋማዊ የአደረጃት መስፈርቶችን ጠብቆ ስለመስራቱ ፣በሂደት ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎችን የሚገልጽ ሪፖርት አዘጋጅቶ ማቅረብ አለበት ።

ሐ/ ፈቃድ ሰጪው አካል ጥያቄው ሲቀርብለት የአመልካቹን የትምህርት ተቋም ተከታታይ የሁለት ዓመት የጥራት ኦዲት ሪፖርት ከመረመረና ተቋሙ አሁን የሚገኝበትን ሁኔታ በስታንደርዱ መሠረት ከገመገመ በኋላ ብቁ ሆኖ መገኘቱ ሲረጋገጥ የሚጠበቅበትን ክፍያ ፈጽሞ የቀድሞውን የእውቅና ፈቃድ በመመለስ ምትክ ፈቃድ ይሰጠዋል።

4.2 የዕውቅና ፈቃድ ስለመሰረዝ

4.2..1 የዕውቅና ፈቃድ የሚያሰርዙ ምክንያቶች

ሀ. የእውቅና ፈቃድ የተገኘባቸው መስፈርቶችን ጥሶ ወይም ከተፈቀደለት የትምህርት ደረጃና እርከን ውጪ እየሰራ ከተገኘ፣

ለ. የዕውቅና ፈቃድ እድሳት ጥያቄ ለፈቃድ ሰጪው አካል ሳያቀርብ የእውቅና ዘመን ተጠናቆ በመስራት ላይ የሚገኝ ከሆነ፣

ሐ. የእውቅና ፈቃዱ የተሰጠው ሀሰተኛ መረጃ በማቅረብ መሆኑ ከተረጋገጠ፤

መ. በተሰጠው ድጋፍና ክትትል ተቋሙ ከነበረበት ዝቅተኛ የብቃት ደረጃ መሻሻል ያላሳየ ከሆነ ፣

ሠ. የተቋሙ ሕጋዊነት መብት ሲፈርስና በፍርድ ቤት ሲወሰንበት ።

4.3 የተሰረዘ ፈቃድን ስለመግለጽ

ሀ/ የእውቅና ፈቃድ ሰጪው አካል በመመሪያው የተደነገጉትን አንቀጾች በመጣስ የዕውቅና ፈቃድ እንዲሰረዝባቸው የተደረጉ የትምህርት ተቋማትን ዝርዝር ፈቃዱ ስለመሰረዙ በመገናኛ ብዙሃን /በራዲዮ፣ በቴሌቪዥን፣ በሕትመት ውጤት/ ሊገልጽ ይችላል።

ለ/ በተለያዩ ምክንያቶች ፈቃዱ የሚሰረዝ የትምህርት ተቋም የትምህርት አገልግሎቱን የሚያበቃው የተጀመረው የትምህርት ዘመን ሲያበቃ ይሆናል።

ሐ/የትምህርት ተቋሙ የዕውቅና ፈቃድ መሰረዝ ተግባራዊ እስከሆነበት ቀን ድረስ በትምህርት ቤቱ በትምህርት ዘመኑ ሲማሩ የቆዩ ተማሪዎች የተከታተሉትን ትምህርት ዋጋ አያሳጣም፣

4.4 የዕውቅና ፈቃድ ማረጋገጫን ስለመመለስ

ሀ/ማኛውም የዕውቅና ፈቃድ የተሰጠው የትምህርት ተቋም ደረጃውን በማሳደጉ ወይም በመለወጡ ወይም በመዋሃዱ አዲስ የዕውቅና ፈቃድ ለማግኘት የቀድሞውን የዕውቀና ፈቃድ መመለስ ይገባዋል።

ለ/የዕውቅና ፈቃዱ የተሰረዘበት ወይም ስራውን ያቋረጠ ማንኛውም የትምህርት ተቋም ሁኔታው በተፈጠረ በአስራ አምስት ቀናት ውስጥ የዕውቅና ፈቃዱ ለሚመለከተው ዕውቅና ፈቃድ ሰጪ አካል የመመለስ ግዴታ አለበት ።

ሐ/የእውቅና ፈቃድ መመለስ ያለበት የትምህርት ተቋም ፈቃዱን ሳይመልስ ለመስራት እየተንቀሳቀሰ መሆኑ ከተደረሰበት አግባብ ባለው ሕግ ይጠየቃል።

4.5 የዳግም ፈቃድ ጥያቄ ስለማቅረብ

ሀ/ የተዘጋው የትምህርት ተቋም በድጋሚ ዕውቅና ፈቃድ ከጠየቀ በዓመቱ መጨረሻ ብቻ እንደ አዲስ ማሟላት ያለበትን የትምህርት ስታንዳርድ አሟልቶ መገኘቱ በባለሙያ ሲረጋገጥና የአ ገልግሎት ክፍያ ሲፈፅም የእውቅና ፈቃድ ይሰጠዋል፣

4.6 ምትክ የዕውቅና ፈቃድ ስለመስጠት

ሀ/ የተሰጠው የእውቅና ፈቃድ የተበላሸበት ማንኛውም የትምህርት ተቋም ምትክ የእውቅና ፈቃድ እንዲሰጠው ሴክተሩን መጠየቅ ይችላል።

ለ/ ለዕውቅና ሰጪ አካል ጥያቄው ሲቀርብ አመልካቹ የተበላሸውን የእውቅና ፈቃድ ከመለሰ በኋላ አስፈላጊውን ክፍያ ፈጽሞ ምትክ ፈቃድ ይሰጠዋል፣

ሐ/ በመጀመሪያ የተሰጠው የእውቅና ፈቃድ የጠፋበት ማንኛውም የትምህርት ተቋም ምትክ የእውቅና ፈቃድ እንዲሰጠው ሲጠይቅ የእውቅና ፈቃዱ እንዴት እንደጠፋ የሚገልጽ የትምህርት ተቋሙ ባለቤት ወይም ህጋዊ ተወካይ የፈረመበት መግለጫና ስለመጥፋቱ የፖሊስ ማረጋገጫ ደብዳቤ ለፈቃድ ሰጪው አካል ማቅረብ ይኖርበታል።

መ/ ፈቃድ ሰጪ አካል የቀረበለትን ጥያቄ መርምሮ የእውቅና ፈቃዱ መጥፋቱን ሲያረጋግጥ ለአመልካቹ ምትክ የእውቅና ፈቃድ ይሰጠዋል።

ክፍል አምስት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

5.1. መመሪያ ስለመተላለፍ

5.2 የተሻሩ መመሪያዎች

5.3 መመሪያው ስለሚሻሻልበት

5.4 መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከ...../2008 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል